# ያንኪዎች ወደ  ሃገራችሁ ሂዱ

አስተያየት
ከተኮላ መኮንን
*Tekola Mekonen*
tekolamekonen@yahoo.com




ይህ ከዚህ በላይ ያለው እርእስ በቅርቡ የታተመው የአቶ አያሌው ይማም YANKEE, GO HOME! የሚለው መጽሐፍ ትርጓሜ ነው። 368 ገጽ የሆነውና በጥቃቅን ፊደላት የተጻፈው መጽሐፍ ቸኩለን በጉጉት የምናነበው አንባብያን ከ 50 ዓመት በላይ መሆናችንን  ደራሲው ግንዛቤ ውስጥ ቢያስገቡ ኖሮ ፊደሎቹን አያሳንሷቸውም ነበር ብዬ ገመትኩ። ለማንኛውም "በራቸውን ክፍት አድርገው ሰው ሌባ  ይላሉ" እንዳልባል በማለት የሚያጎላ መነጽር ገዛሁና ማንበቡን ተያያዝኩት።

አቶ አያሌው ይማም ላበረከቱት የስነጽሑፍ አስተዋጽኦ እንደ አንባቢ ከልብ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ጥረታቸው የተደበቀውን ታሪክ ላንባብያን ማሳወቅ ነውና እንዳሰቡት ግባቸውን የመቱ ይመስለኛል። ይህንን የግል ታሪካቸውን ሲተርኩን ደስ የሚል ትዝታ እየቀሰቀሰባቸው እንደ ፈነደቁ ሁሉ፡ ጨለማውን የስቃይ ወራትም እያሰቡ ዳግመኛ እየቆሰሉ እንደ ከረሙም መገመት አያዳግትም። እንደ ግለሰብ ብሎም በወቅቱ እንደ ወጣት ታጋይ ለደረሰባቸው ሁሉ የአካልና የመንፈስ ቁስል ከልብ እያዘንኩ ለጥንካሬአቸው አድናቆቴን ስገልጽ ለደረሰባቸው ግፍ ግን ሁላችንም ልናደርግላቸው የምንችለው  ነገር ቢኖር ይቅርታ  ማለት ብቻ  ይሆናል እኔም ይቅርታ ከልብ አዘንኩ እላቸዋለሁ። ይህንን ስቃይ ያደረሰባቸው ድርጅትም ላለፈ የተደበቀ የሰንገደ  ግፋዊ ድርጊቱ ባደባባይ ይቅርታ ሊጠይቃቸው ይገባል። የድርጅት ንቃትና ብስለት የሚለካው መጭውን ችግር በመተንበይ፣ ያየውን ችግር በማጋለጥ፣ በመቃወምና  የትግል እቅድ አውጥቶ በማታገል ብቻ  ሳይሆን የሰራውንም ጥፋት አምኖ  በመቀበል ላይ ነውና።

YANKEE, GO HOME ን መጀመሪያ ሳየው የተሰማኝ ነገር ቢኖር ለምን ደራሲው ይህንን አርእስ መረጡት የሚል ነበር። የተማሪው ንቅናቄ በወቅቱ አንግቦት የነበረውን መፈክር ለማስታወስ እንደሆነ ለማወቅ ደግሞ እሳቸውን መጠየቅ አላስፈለገኝም። ነገር ግን እንደ እኔ ከትዝታውና ከእውነታው የበለጠ አርእስቱ ትንሽ የሚያስበረግግ ሆነብኝ። በተለይ ከሽፋኑ ቀይ ባንዲራነትና ከተደረደረው ካላሽንኮቭ ጋር ሲጣመር ያልኩትን ፍርሃቴን አጎላው። ከፍ ብዬ ልጠቁም እንደ ሞከርኩት ደግሞ መጽሐፉን ገለጥ ሳደርገው የእትምቱ ማነስ ለጊዜውም ቢሆን አስቆጣኝ። ማንበቡን ተያያዝኩት። ጎብኝቼው የማላውቀውን ወሎን በአቶ አያሌው ገለጻ ያደኩበት መንደር እስኪመስለኝ ድረስ ፈነጠዝኩበት። አብሬአቸው ጠላ ቤት ቡና ቤትና አዳሪ ትምህርት ቤት ብሎም በበቅሎ ጀርባ ተፈናጥጬ ገጠሩን ጎበኘሁ። የልጅነታቸው ከጅብ ጋር ፍጥጫ የእኔን የልጅነት ሌላ ትውስታ ሁሉ ቀሰቀሰብኝ። ጥሩ የማይረስ አእምሮ እንዳላቸውም ተገነዘብኩ።

አቶ አያሌው ከወሎ ወደ አዲስ አበባ ዩንቨሪስቲ ተማሪ ሆነው ከመጡ በኋላ አዳሪ ሆኖ ለመማር ጊዜ አልፈጀባቸውም። ለምን ቢሉ ወሎ ባዳሪ ት/ቤት መቆየታቸው ጥሩ ተመክሮ ሰጥቷቸው ነበርና ነው። አቶ አያሌው ብዙውን ሲነግሩን የቆየቱ የራሳቸውን የትግል ጉዞ ነውና ስለራሳቸው የተረኩትን እንዳለ እየተቀበልኩ በሰባ ደረጃ በአፍንጮ በር ማታና ቀን ያደረጉትን የልጅነት ሥራ ጊዜ ፈጅተው ቃል በቃል የተመላለሱት ሳይቀር ባይነግሩን እንደኔ የተሻለ ነበር እላለሁ። በአንጻሩ በዩንቨርስቲ ውስጥ በወቅቱ የተነሱትን ውይይቶች እንዳለ ቢያቀርቡልን ኖሮ መልካም ይሆን ነበር ብዬ እገምታለሁ። ለምን ቢሉ የጸሐፊው ጥረት የነበረውን የወጣትነት የትግል ተመክሮ ለማካፈል ነውና።

ጎንደር አስተማሪ ሆነውም ይሁን የወሎ ግብር ተማኝ ብሎም ኤርትራ በመምህርነት ብዙ የነገሩን ከፍቅረኞቻቸው ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ነው። እኔ ፍቅረ ጥላቻ አድሮብኝ ሳይሆን ማወቅ የምፈልገውና የሳቸውም ትልቁ መልእክታቸው የትግል ሕይወታቸውን ታሪክ ሊነግሩን የተነሱ በመሆኑ ትኩረቱ እሱ ላይ መሆን ነበረበት እላለሁ። አቶ አያሌው ያላቸው የማስታወስ ችሎታ የሚደነቅ ሆኖ ማግኘቴን መደበቅ ግን የሚቻለኝ አልሆነም። በልደት አዳራሽ በዩንቨርስቲ ምግብ ቤት (CAFETERIA) የነበረውን የወቅቱን የተማሪ አመጽና ከፖሊስ ጋር የነበራቸውን ግብግብ ቃል በቃል በስእላዊ መንገድ ሲገልጹ ድርጊቱ ትላንት የተደረገ ያስመስሉታል። በስብሰባ ላይ የተደረጉ የቃላት መለዋወጦችን ጭምር እንዴት አስታወሱ ብዬ ባለፈው በስልክ ስጠይቃቸው የሰጡኝ መልስ ይበልጡን አስደነቀኝ። <u>"መጽሐፉን የጻፍኩት ሜዳ በኢሕአሰ እስር ቤት እያለሁ ነበር" ብለው መለሱልኝ።</u> እንዴውም አሉ አቶ አያሌው <u>"ብዙ ቀንሼና ቆርጬ ከመጽሐፉ ያወጣሁት ያልተነገር እራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ አለ"</u> ሲሉኝ ቀጣዩን በጉጉት እንድጠብቅ አደረጉኝ።

ይህንን ካልኩ በኋላ አቶ አያሌውን የምጠይቃቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ይኖሩኛል።

1 ድርጅት ወይንም የሚያውቁትን ሰው ፍለጋ አስመራ ሕይወትን አደጋ ላይ ጥሎ መንከራተት ምን አመጣው?

2 በእግር በፈረስ መፈለጋቸውን እያወቁ አዲስ አበባ ተመልሶ መሄድ ምን ማለት ነው?

3 በአንድ ተማሪ ፈቃድ ከ ELF ጋር ግንኙነት መፍጠራቸው ሳይሆን ባፋጣኝ ባለስልጣናትን ማግኘት ከቻሉ ደርጅቶቹንም እነሱ ሊያገናኟቸው ይችሉ አልነበረም ወይ? (ይህንን ልል የወደድኩት እሳቸው በነበሩበት በዚያን የሁለተኛ ፈጻሚት ሽማግሌ ወቅት ባርካ ነበርኩና ነው ጥያቄውን ለማንሳት የወደድኩት)

4 ከካርቱም ድረስ ትግራይ መጥተው የኢሕአሰን ሰራዊት ተጋዳዎች ለደቂቃ አውርተው ተመልሰው ወደ ሱዳን ለምን ሄዱ?

5 በሳቸው አመለካከት ELF አመራሮች ለምን ለሳቸው ቸርና ለጋስ የሆኑ ይመስላቸዋል የሚለውን? ልጠይቃቸው እወዳለሁ።

በተጨማሪ አቶ አያሌው ይማም ምስላቸውን ቢለጥፉልን ኖሮ የበለጠ መልካም ነበር ብዬ ሃሳብ መሰንዘር እወዳለሁ።

የአቶ አያሌው ይማም ይህ የትግል ሕይወት ታሪክ በሞላ ጎደል የተማሪውን ትግል ውድቀትና ጥንካሬ የሚያሳይ፡ ያልተነገሩ የድርጅቶች ጨለማን አሳፋሪ ጎን የሚዳስስ በመሆኑ ትልቅ ትምህርት ልናዳብርበት የምንችል መጽሐፍ ነው። በአቶ አያሌው መጽሐፍ ቁጭት እንጂ ቂም ባለማየቴ አደነቁቸው። እኔ ብሆን ምን ይሰማኝ ነበር? ብዬ እራሴን ስጠይቅ ትልቅነታቸውና የንቃተ ሕሊና ልዩነት ቁልጭ ብሎ ታየኝ። በማጠቃለያ ልል የምወደው ነገር ቢኖር በግፍ የተገደሉትን ስናስብ ስንቆጭ የዛኑ ያክል በደረሰባቸው ግፍ በእየለቱ እየሞቱ የሚነሱትን እንደ አቶ አያሌው ይማም አይነቶችንም እያሰብን የሕሊና ጸሎት ማድረግ እንዳለብን ነው።

መጽሐፉን ለመግዛት ለምትፈልጉ ወደ አማዞን በመግባት ማዘዝ እንደሚቻል ማወቄን ስነግራችሁ የመጽሐፉ ዋጋ ከፖስታ ቤት መላኪያ ጋር $23 የአሜሪካ ብር መሆኑን ለማረጋገጥ ችያለሁ። በቀጥታ ለመገናኘት ለምትፈልጉ አድራሻቸው

AYALEW YEMAM (MUKHTAR)
P.O.BOX 11112
TAKOMA PARK, MARYLAND 20913
ayimam@verizo.net